- 35 -

ሙስሊም ሁን ፤ ግና ሚዛናዊ ሙስሊም

በ2004ቱ የአሜሪካዊ የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ከርከር ወቅት ሴናተር ጆንኬሪ ምሽቱን የቀኑን የሽንፈት ውሎውን ለመካስ አድርጎ ተጠቀመበት። ከቀረቡለት ጥያቄዎች መካከል የመጀመርያውን ሲመልስ አሜሪካ "አክራሪ እስልምናን የሚያራምዱ" ሙስሊሞችን ማግለል እንዳለባት ገለጸ።

"በሸብርተኝነት ላይ የተጀመረውን ዘመቻ ለመዋጋት እኔ የተሻለ ዕቅድ አለኝ። ... መጀመር ያለብን አክራሪ እስልምናን የሚያራምዱ ሙስሊሞችን በማግለል ነው። በአሜሪካ ውስጥ እነሱ ሊኖሩ አይገባም።" አለ።

መጀመርያ ላይ ንግግሩ ያው የተለመደ ንግግር ተደርጎ ነበር የተወሰደው። ከተማረ ሰው የማይጠበቅ ዓይነት ንግግር። በመሠረቱ "ሙስሊም" ማለት ትርጉሙ "የኢስላምን ሃይማኖት የሚከተል" ማለት ነው። ስለሆነም "ኢስላማዊ ሙስሊም" ማለት "አሜሪካዊ አሜሪካኖች" እንደማለት ነው። እና ኬሪ ይህን ሲል እየደጋገመ ነውን? ወይስ የሚናገረውን ነገር ተረድቶ ይሆን? ሁሉም ሙስሊሞችስ "ኢስላማዊ" ናቸውን? በርግጥ የሚለው አይደለም እውነቱ። በትንሹ ሁሉም ሙስሊሞች ጥሩዎች አይደሉም።

ኢስላም ችግር እንደሆነ ብዙ አስተያየቶች ይደመጣሉ። ኢስላም እንደ እምነት የአክራሪነት ምንጭ ከሆነ፤ በመጠኑ "ኢስላማዊ" መሆን የተሻለው ኢስላም ነው። ግና እነሱ "ሚዛናዊ /መካከለኛ/ Moderate/ ሙስሊም የሚሉት ስሙን ብቻ የያዘውን ሙስሊም ነው። በመጠኑ መጥፎ የሆነ እንደማለት። ይህን ማለት አንድን ጥቁር የሆነን ሰው ነውጠኛ ነው እንዳይባል በመጠኑ ብቻ "ጥቁር ሁን" እንደማለት ነው። እንዲሁ "ኢስላማዊ" የሆነን ሙስሊም "አክራሪ እስልምናን የሚያራምድ" ነውና መገለል አለበት ማለትም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው። "በመጠኑ ብቻ ሙስሊም ይሁን" እንደማለት።

ሙና ሞይፊል በስፔኑ የቦንብ ፍንዳታ ተሳትፏል ተብሎ በሐሰት የተወነጀለውን ባሏን ስትገልጽ የገለጸችበት ሁኔታ ይህንኑ መርሃቸውን የተገነዘበች ይመስላል። ስለ ባሏ ከአክራሪነት ንጹህ መሆን ምስክርነቷን ስትሰጥ እንዲህ ብላለች:-

"እኛ ቤታችን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ አለን። እሱ አክራሪ አይደለም። እሱ ይህን ሲያረግ የተለየ እና ልዩ የሆነ ነገር እንደሆነ አድርጎ ነው ያሰበው።" ሜይፊልድ ስለ ባሏ ወደ እስልምና መግባት ለአሶሼትድ ፕሬስ ስትናገር ነበር ይህን ያለችው።

CamScanner

CamScanner

የሱን ንጽሕና ለማረጋገጥ ብላ ነው ሚይፊልድ ባሏ ለሃይማኖቱ ለኢስላም ስላለው ታማኝነት ደረጃ ለማስረዳት የሞከረችው። ሌላው ቀርቶ የሱ ወደ እስልምና መግባት የሱ ብቻ ወንጀል እንደሆነ ነው ለማሳመን የፈለገችው።

የመስጊድ አስተዳደሩ ሸህሪያር አሕመድ ሚይፊልድን ለመከላከል ተመሳሳይ አካሄድን የተከተለው "መካከለኛ/ሚዛናዊ ሙስሊም ሆኖ ነው የሚታየው" በማለት አስረድቷል። አሕመድ ለሪፖርተሮች ሲያብራራ አሕመድ ወደ መስጊድ ሲመጣ ያየበትን ሁኔታ እንዲህ ይገልፃል "ሚይፊልድ ለጁምዓ ሶላት ሲመጣ ጫማውን በረንዳው ሥር ነበር ያደረገው፣ ከዚያ ባዶ እግሩን ታጠበና ስብከት ለመስማት ምንጣፉ ላይ ተቀመጠ።አምስቱን ሶላቶች መስጊድ ከሚሰግድ ጠንካራ ሙስሊም እንደማያስመድበው ነው።" ብሏል በሀሳቡ።

እዚህ ጋ የምናስተውለው ነገር ሚይፊልድ ወንጀለኛ አሊያም ንፁህ ይሁን የሚረጋገጠው በቀን ስንት ጊዜ ጀማዓ መስጊድ ይሰግዳል የሚል መነሻ ያለው ተይዞ መሆኑ ነው። በአሕመድ እይታም በዚህ መልኩ ሁኔታው ተገምግሞ "ስለ ሃይማኖት እምብዛም ነው" ከሚል ውሳኔ ተደርሷል።

ስለ ሃይማኖት ብዙም የማይጨነቅ ሙስሊም የዚህ ዓይነቱን ሙስሊም ነው ሚዲያዎች ትከከለኛና ተቀባይነት ያለው ነው ብለው የሚያራግቡለት። የሚዲያ ባለቤት እና የ"The Trouble with Islam" መጽሐፍ አዘጋጅ የሆነችው ኢርሻድ ማንጂ የነኚህ ዓይነቶቹ ሚዲያዎች ካገነኗት ውስጥ አንዷናት። ማንጂ ትልቅ ዕውቅና ያላት፣ ስለ ሚዛናዊ በስፋት የሚነገርላት፣ በትላልቅ ሚዲያዎች ላይ ጭምር የቀረበች እንስት ናት። ሌላው ቀርቶ የታዋቂዋን የሾው የባለቤት የኦፐራን የቹትፓህን የ"gutsiness" ሽልማት እስከማሸነፍ ደርሳለች።

ማንጂ ራሷ ሙስሊም አማኒ አድርጋ የምትገልጽ ሲሆን ሚዲያዎች ግን "የተግባር ሙስሊም" አብነት ናት ይሏታል። የአሜሪካ የሰላም ተቋም የቦርድ አባል ዳንኤል ፓይፕስ "ደፋር፣ መካከለኛ እና ዘመናዊ ሙስሊም" በማለት ይገልፃታል። የሚገርመው ግና ከማንጂ ሀሳብ ይልቅ የፓይፕስ ሀሳብ ለሰላም ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑ ነው። የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ ሶላት ከእስልምና ማዕዘናት አንዱ ስለመሆኑ የማንጂን ሀሳብ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡-

"መስገድ የጀመረችው በራሷ ነው፣ እግሮቿን፣ ክንዶቿን እና ፊቷን ከታጠበች በኋላ ሰፊ ልብሷን ለብሳ ወደ መካ ፊቷን በማዞር ትቀመጣለች። ግና በሂደት ግን ይህንን ማድረግም ትታለች። ምክንያቱም አዕምሮን የማያሳምን ነገር መከተልና በልማድ መጎተትን ስለማትፈልግ ነው።" ብሏል።

CamScanner

CamScanner

ማንጂ ይህን ሀሳቢን ዓለም ላይ ከ2 ቢሊዮን በላይ ለሚሆኑ ሰዎች አስተላልፋለች። ይህንና መሰል የአምልኮ ተግባራትን እንዲተው ተጣርታለች። ማንጂ እንደ መሰገድ እንደማትፈልግ አንድ ትርጉም የሌላት ሴት መገለጽ የለባትም። እንደ አንድ የነፃነት ታጋይ ከእምነቱ ማዕዘናት መካከል አንዱ የሆነውን ሶላትን ለመተው የደረሰችበት የራሷ ውሳኔ ነው። እንደነሱ ድጋፍ - ይህ አምባገነንነትን ከመታገል አንፃር የወሰደችው እርምጃ ነው። ያመፀችበት እምነት ደግሞ እስልምና ነው። ስለዚህም መበረታታት አለባት። ምክንያቱም እሷ ደፋር እና ብርቱ ናትና። ሌሎች እስልምናን አጥብቀው እንዳይከተሉ ሞዴል ናት።

የዚህ ዓይነቱን ሞዴል ለሙስሊሙ ማስቀመጥ አንድን ሰው "በጣም ጥቁር" ወይም "በጣም አይሁድ" እንዳይሆን እንደመጠየቅ ነው። እንዲህ መሆን እንደ መጥፎ አሊያም እንደ ነውጠኛ አድርጎ ያሳስባል ለማለት ነው እንዲህ የሚሉት። "መካከለኛ ጥቁር" ወይም "መካከለኛ አይሁድ" ለመሆን የሚጥር ብቻ ነው እንደ እውነተኛ የነፃነት ታጋይ ተደርጎ የሚታሰበው። ለምሳሌ ማንጂ ለዋሽንግተን ፖስት እንደነገረችው "ሁከት መቀስቀሱ አይቀሬ ነው። ስለዚህ ለነፃነት ሲባል እንዲሆን ለምን አይደረግም።" ብላለች።

አዎን ነፃነት ጥሩ ነው። ማንጂም በራሷ እምነት በትክክል ብላው ይሆናል። ኬሪ ደግሞ በተሻለ መልኩ ገልፆት ይሆናል። ግና የካሊፎርኒያው የኢምፔርያል ቫሊ ኮሌጅ ቢዝነስ አስተዳደር ፕሮፌሰር ደግሞ የነርሱን ድብቅ ፍላጎት እውነታውን ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል - እንዲህ በማለት "ኢስላማዊ ሽብርተኝነትን ለማጥፋት ብቸኛው መንገድ የእስልምናን ሃይማኖት ማጥፋት ነው።"

CamScanner

CamScanner

- 36-

አሳዛኙ እና መናገሩ የሚከብደው የሕዝበ ሙስሊሙ ሁኔታ

በሰው ልጅ ጭንቅላት ውስጥ የምንሄድበት ቦታ ሲጠፋን የሆነ የምንደበቅበት ቦታ ያለ ይመስኛል። አንዳንድ አሳዛኝ ነገሮችን የምናስተናግድበትና ብሶታችንን የምንተነፍስበት የልብ ክፍል ያለንም ይመስለኛል። ዛሬ ላይ ግና በተለይ ለሶርያ እና ለፍልስጤም ሕዝቦች እየሆነ ያለው አሳዛኝ ነገር በአዕምሮ የሚስሉት እና በልብ የሚቀርፁት ምናባዊ ስዕል ብቻ አይደለም። እነርሱ እየኖሩት ያለ ተጨባጭ እውነታ እንጂ።

በዚህ ምድራዊ ደሴት ላይ እየሆነ ያለውን እልቂት በተስፋ መቁረጥ ስሜት እንደምከታተለው ሁሉ፤ እንዲሁ በሌላ በኩል ደግሞ ወዴት እንደምሄድ ግራ የተጋባሁ ሆኛለሁ። ለዚህም ይመስለኛል በአዕምሮዬ ውስጥ ስለዚህ ስለሚያስጨንቁኝ ጉዳዮች እየተከሰቱ ስለመሆናቸው የሚያስረሳኝና ምስል የማይሠጠኝ ቦታ ቢኖረኝ እላለሁ። በሐዘን፣ በቁጣ፣ በጭንቀት እና በቁጭት ውስጥ ከቆየሁ በኋላ በመጨረሻም ማለቂያ የሌለው ጥያቄ እጠይቃለሁ።

ይህ ሁሉ ለምን ሆነ? እላለሁ

ለምን?

በኛ ላይ ይህ ለምን ሆነ? በዓለም ላይ ስቃያችን የበዛው ለምንድነው? ይህንን ሰቆቃ ለማቆም ያልቻልንበት ምክንያቱ ምንድነው? የአገሬው ዜጋ በሆንንበት ሁኔታ በአገራችን ጭምር እኛ ሙስሊሞች ተጽእኖችን ያነሰው ለምንድነው? ያለ አሜሪካ ተጽእኖ እኛ ሙስሊሞች ምንም ማድረግ የማንችል ባይተዋሮች የሆንንበት ምክንያቱ ምንድነው? ለምንድነው ይህን ያህል የወረድነው? ለምን? ለምን ... ብለን? ብዙ እያልኩ ብዙ ጥያቄዎችን እጠይቃለሁ።

ለምን? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል።

ቆም ብለን እንደ ሙስሊም ማኅበረሰብ የት እንዳለን መፈተሽ ይኖርብናል። የሆነ ጊዜ ሙስሊሞች መላውን ዓለም የተቆጣጠሩበት ሁኔታ ነበር። ያኔ ታዲያ በወዳጅ ዘመድ ይወደዱ፤ በጠላቶችም እጅግ ይፈሩና ይጠሉ ነበር። ዛሬ ላይ ግን ከማንም በላይ ጥቃት የሚደርስበት የሚወነጀለውና እና የሚጠላው ሙስሊሙ ነው።

በቅርብ ጊዜ በተደረገ ዳሰሳ ከሀምሳ በመቶ በላይ የሚሆኑ አሜሪካውያን ስለ ኢስላም ያላቸው አመለካከት ጥሩ እንዳልሆነ ነው። አርባ ሦስት በመቶ የሚሆኑት ደግሞ

CamScanner

CamScanner

ከክርስቲያኖች፣ ከአይሁዶችና እና ቡድሃዎች በበለጠ እጥፍ ቢያንስ ለሙስሊሞች ድብቅ የሆነ ጥላቻ አላቸው።

በርግጥም በበርካታ ቦታዎች ላይ ሙስሊሙ ላይ የሚደርሰው ጥላቻ ብቻ አይደለም። ለስቃይና ለግድያ መዳረግም ጭምር እንጂ። አንድ ሙስሊም ሙስሊም በመሆኑ ብቻ ማንነቱን ይነጠቃል፣ ለመከራና ስደት ይዳረጋል። በሐሰት ይወነጀላል። ይታሰራል። በተለያዩ አካባቢዎች ሙስሊም ጠልነት በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቷል። አንዳንድ አገራት ላይ በአከራሪ ፖለቲከኞች የንግግር አጀንዳ ሁሉ የሆነበት ሁኔታ አለ። የሙስሊሙን ጉዳይ ለፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያቸው ይጠቀሙበታል።

ይህ ሁኔታችን ነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ከ1400 ዓመታት በፊት ከተነበዩት ሁኔታ ጋር ይመሳሰላል፡-

"አውሬ በግዳዩ ላይ እንደሚጠራራው ሁሉ ሕዝቦች ይጠራሩባችኋል።" አሉ። "ያኔ በቁጥር አንሰን ነው ወይ?" አላቸው አንድ ሰው። "አይደለም በቁጥር ብዙ ናችሁ። ግና እንደባህር ላይ ዐረፋ ናችሁ።" አሉት። አላህ ጠላቶቻችሁ እናንተን እንዳይፈሩ ከልቦቻቸው ፍራቻን ያስወግዳል። በናንተ ልቦች ውስጥ ደግሞ ፍራቻን ይለቃል።" አሉ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የልቦና ፍራቻ ድከመት ምንድነው?" አላቸው። "ይህችን ዓለም ትወዳላችሁ። ሞትን ትጠላላችሁ።" አሉ። (አቡ ዳውድ እና ኢማም አሕመድ እንደዘገቡት)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደተነበዩት፤ ሕዝቦች እኛን ለማጥቃት ምርጥ ምግብ እንዳገኘ ተኩላ መንጋዎቻቸው ጋር ይጠራሩብናል። በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እኛን በባህር ላይ ዐረፋ ነው የመሰሉት። ዐረፋ ምንም ዋጋ የለውም፤ እርባና ቢስ ነው። ምንም ነገር መቋቋም አይችልም። በአንዲት ትንፋሽ ድራሹ ይጠፋል። በራሱ ምንም ነገር ማድረግ የማይችል ነገር ነውና። ውሃ ነው ወዲህ እና ወዲያ የሚያመላልሰውና የሚጫወትበት።

ይህ ተጨባጭ ሁኔታችን ነው። እርሳቸው እኛን የገለፁበት ተጨባጭ። ግና ለምን ይህ ሆነ ብለን መጠየቅ መቻል አለብን። እርሳቸውም ልብ በወህን (ድከመት) ትሞላለች አሉ። ስለ ወህን ምንነትም ሲጠየቁ ይህችን ዓለም አብዝቶ መውደድ እና ሞትን መጥላት እንደሆነ ተናገሩ። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እዚህ ላይ ማመላከት የፈለጉት በዱንያ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ስለሰጠሙ ሰዎች ነው። ዱንያን አብዝተው ወደዱና ስግብግብ፣ ቁስ አምላኪ፣ ማገናዘብ የማይችሉ፣ እና ከአላህ ጋር ለመገናኘት ጉጉት የሌላቸው አደረገቻቸው። እነኚህ ሰዎች በዓለማዊነት ተውጠው ምንም ዓይነት የሞራል ሥነምግባር የሌላቸው ናቸው።

የዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ነው የሰዎችን መልካም ሥነምግባር የሚቀይረው። ይህ ሁኔታ ነው

CamScanner

CamScanner

ሰዎችን ከጥሩ ወደ መጥፎ፤ ከመጥፎ ወደ ጥሩ የሚቀይራቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوْمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُوا۟ مَا بِأَنفُسِهِمْ ۗ وَإِذَآ أَرَادَ ٱللَّهُ بِقَوْمٍ سُوٓءًا فَلَا مَرَدَّ لَهُۥ ۚ وَمَا لَهُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَالٍ﴾

«አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ኑኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም። አላህም በሰዎች ላይ ክፉን በሻ ጊዜ ለእርሱ መመለስ የለውም። ለእነርሱም ከእርሱ ሌላ ምንም ተከላካይ የላቸውም።» (አር-ረዕድ : 11)

ስለሆነም በባህሪያቸው መቀየር ምክንያት አላህ የሰዎችን ሁኔታ ይቀይራል። ከግዙፍ ኃይል ወደ ትንንሽ ዐረፋ ያወርዳቸዋል። ልባቸውና ባህሪያቸው የተስተካከለ እንደሆነ ደግሞ ባዶ ዐረፋ የነበረውን ማንነታቸውን ወደ ኃያልና ፅኑ ይቀይራቸዋል።

ስለሆነም እኛ ሙስሊሞች ተስፋ መቁረጥ የለብንም። አላህ ድል ሊሠጠውና የበላይ ሊያደርገው ለዲኑ ቃል ገብቷል። ጥያቄው እኔና አንተ የዚህ አካል ነን ወይ? የሚለው ነው። አላህ በቁርኣኑ ውስጥ እንዲህ ይለናል -

﴿وَلَا تَهِنُوا۟ وَلَا تَحْزَنُوا۟ وَأَنتُمُ ٱلْأَعْلَوْنَ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ﴾

“እናንተም የበላዮች ስትኾኑ ምእመናን እንደኾናችሁ ስትስነፉ፤ ስትዘኑም።”
(ኣሊ ዒምራን : 139)

በእውነተኛ እምነታችን እና በጥረታችንና ትግላችን ብቻ ነው አላህ (ሱ.ወ.) ሁኔታችንን ሊቀይርልን የሚችለው። ሶርያ እና ፈለስጢን እንዲሁም በመላው ዓለም ለሚገኙ ሙስሊም ወንድሞቻችን ስንል እንኳ እኛ ሙስሊሞች መንቃት እና ወደ አላህ መመለስ ይኖርብናል።

CamScanner
CamScanner